# ያ ትውልድ

የ«ያ ትውልድ ተቋም» ልሳን

ያ ትውልድ ቅጽ 2 ቁጥር 2 የካቲት ፳፱ ቀን ፪ ሺህ ፯ ዓ.ም.

## <u>ከእናቶች ለእናቶች</u>

*(ማርች 8 ዓለም አቀፍ የሴቶች ቀን 104ኛ ዓመት ምክንያት በማድረግ)*

**ለማርች 8 ዓለም አቀፍ የሴቶች ቀን እንኳን አደረሳችሁ። ሴቶች በሴትነታቸው ዝቅ ተደርገው በማህበራዊ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ተሳትፎአቸው የሚደርስባቸውን አድሎና የወንድ የበላይነትን ለመቋቋምና መብታቸውን ለማስከበር ድምጽ ያሰሙበት ዓለም አቀፋዊ የትግል ቀን 104ኛ ዓመት ማርች 8, 2015።**

**የማርች 8 ክብረ በዓልና የንቅናቄው ታሪክ በሀገራችን ብቅ ያለው የካቲት 1966 ዓ.ም.ን ሕዝባዊ አመጽ አስታኮ ነው። ሴቶችን በማጀት አሥሮ ያስቀረው የባላባት ሥርዓት ላይ የተቀጣጠለው ሕዝባዊ አመጽ የሴቶችን ጥያቄ ይዞ ብቅ ማለት ብቻ ሳይሆን ሴቶችን የትግሉ ተሳታፊና አንቀሳቃሽ ሞተር አድርጓል። ሴቶች በእውቀትም ሆነ በችሎታ እንዲሁም በአመራር ብቃታቸው ከወንድ እኩል ብቻ አይደለም ልቀውም ቢታዩ በሥርዓቱ ተንቀውና ተገፍተው ኖረዋል። እንደማንኛውም ዜጋ ከሚደርስባቸው አስከፊ ጭቆና በደልና መብት እረገጣ በተጨማሪ በሴትነታቸው ብቻ የሚደርስባቸውን በደልና እንግልት ለማሸነፍና ማንነታቸውን ለማሳየት ያልታከተ ጥረትና ተጋድሎ ማድረጋቸውን የትላንት ታሪካቸው ይመሰክራል።**

**በሀገራችን ኢትዮጵያ የእናቶቻችን የእንግልት ኑሮና ሕይወት የቅርብ ጊዜ ትዝታ ብቻ ሳይሆን ዛሬም ያለ ነው። ለሽክም ሲሆን ተመራጭና ጠንካራ መሆናቸውን ውኃ በእንስራ፣ ማገዶና ሚፈጨውን ጥራጥሬ በጀርባ ተሸክመው ቤተሰቡንና ማህበረሰቡን ቀጥ አርገው ይዘዋል። ለእንጨት ፈለጣው፣ ለልብስ አጠባው፣ ለቤት ጽዳቱ ወደር የሌለው ጉልበታቸው ለፋብሪካ ሥራው ግን ዝቅ አድርጎ ዝቅተኛ ተከፋይ ያደርጋቸዋል። የቤት ጉልበታቸው ለአደባባይ ይናቃል። ይህ ነበር የብልሹ ሥርዓት ውጤት። ዝቅተኝነታቸውን ይቀበሉ ዘንድ ብዙ ተተርቶባቸዋል። የቤተሰብ ሕይወት ዋልታነታቸውን አደባባይ ለማውጣትና ማንነታቸውን ለማሳየት ሴቶች እህቶቻችን መከራን ተጋፍጠዋል፣ መስዋዕትነትን ከፍለዋል። ዛሬ ዓለማችን ለሴቶች ያላት ቦታ ከፍ ያለ ቢሆንም አሁንም ትግልን ይጠይቃቸዋል። ዛሬ ለ104ኛ ጊዜ በዓለም ደረጃ የሚከበረው ዓለም አቀፍ የሴቶች ቀን ሴቶች በፆታቸው ምክንያት የሚደርስባቸውን አድልዎ ለማስቆም የተከፈለ የመስዋዕትነትና የድል ቀን ነው።**

